

Scanned with CamScanner

፩. ለተፈጥሮትከ ። መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል ሆይ በዕለተ እሑድ ለተከናወ ነው ተፈጥሮህ ሰላምታ ይገባል ። አስቀ ድሞ ከነፋስና በእሳት ለተፈጠረው ሥነ ገጽህም ሰላምታ ይገባል ። መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል ሆይ የሦስቱ ነገደ መላእክት አለቃቸው አንተ ነህ ። እንደገናም ዮሐንስ ወልዱ ንጉድጓድ እንደተናገረው የሰውን ሁሉ ማጎፀን እንድትፈታ ተሾምክ ።

፪. ለገዘረ ሰምከ ። መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል ሆይ አዳም አዳምን ሳይባል በፈጣሪ አፍ አስቀድሞ ለተጠራው ስም አጠራርህ ሰላምታ ይገባል ።

መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል ሆይ ሰላምን የሚያፈራ መንፈስ ቅዱስ ዕውቀትንና ከዓቅም በላይ የሚሆን አምላካዊ ጥበብን ምላብኝ ።

፫. ለስእርተ ርእስከ መልአኩ ቅዱስ

Scanned with CamScanner

ሩፋኤል ሆይ በአምላክ ጥበብ ለተሠራው የራስ ጠጉርህ ሰላምታ ይገባል ። ከመልክ በላይ ለወጣው ጠጉርህም ሰላምታ ይገባል ።

መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል ሆይ የመጽሐፉ ቃል እንደተናገረ ወለተ ራጉኤል ከበሽታዋ ዳነች ። ታውሮ ይኖር የነበረ ጦቢትም ብርሃን አየ ።

፬. ለገጽከ ። መልአኩ ቅድስ ሩፋኤል እግዚአብሔር ለስራው ፊትህ ሰላምታ ይገባል ። በመቃራረብ ለሚታዩ ቅንድቦችህም ሰላምታ ይገባል ።

መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል ሆይ የነፍሴ ጠላት ዲያብሎስን በከንፈረድዔትህ ታሰንካክለው ዘንድ ከመ ኖርህ የተነሣ መገሠፃችን አትተው በሩንም ይዘህ በጥፋት ውስጥ ጣለው ።

፭. ሰላም ዕብል ለአዕይንቲከ ። መልአኩ ቅድስ ሩፋኤል ሆይ ለሚያስደስቱ ዓይኖችህ ሰላምታ ይገባል ። ለመለመን ለተሰ

Scanned with CamScanner

በሰቡ ጆሮችሁም ሰላምታ ይገባል የሕይ
ወት መልአክና መንፈሳዊ መልአክ
ቅዱስ ሩፋኤል ሆይ የኃጢአቴን እሾህ
በየጊዜው በየሰዓቱ ሁሉ አቃጥልልኝ
አንተ ነበልባላዊ እሳት ነህና ።

፮. ለመላትሒክ መልአኩ ቅዱስ
ሩፋኤል ሆይ አንድነታቸው ነበልባል
ለሚሆኑ ጉንጮችህ ሰላምታ የይቅርታ
መዓዛ በሮች ለሚሆኑ አፍንጫዎችህም
ሰላምታ ይገባል ።

ከባዕለ ደግነት ይልቅ ችግርን
የመረጠ የጥፋት መልአክ ዲያብሎስን
ቦማይፈታ ገመድ ከኮረብታ በታች
ያሠረከው መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል
ሆይ ከመውደቅና ከጥፋት ደግፈኝ ።

፯. ለከናፍሪክ ። መልአኩ ቅዱስ
ሩፋኤል ሆይ ምስጋናን ለማያሰልሱ
ከንፈሮችህ ሰላምታ ይገባል ። የተመሰ
ገኑት የሥላሴ ምሥጢርን ለሚያመሰግን
አፍህም ሰላምታ ይገባል ። አንተ የመ

Scanned with CamScanner

ንፈስና የሕይወት መልአክ ቅዱስ ሩፋኤል ሆይ መዳን እንጀራን ከደ ስታ ወይን ጋር እሸከም ዘንድ እኔን ባሪያህን ሁልጊዜ መማበኝ ።

ሯ. ለአስናኒከ መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል ሆይ የሚያስፈራ የመልአክ ጥር ሶች ለሚሆኑ ጥርሶችህ ሰላምታ ይገባል። የአማረ የመለኮት ሥራ ለሚሆን አንደ በትህም ሰላምታ ይገባል ከሥጋና ከደም የራቅህ መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል ሆይ የት ረገመ የኃጢአት አውሬ ዲያብሎስ መጥ መድ እንዳያሰናክለኝ አፌ ደካማው ባሪ ያህ በአንተ ኃይል ቆራርጭ ልጣለው ።

ፀ.ለቃልከ። መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል ሆይ እንደ መብረቅ ለሚሰማው ቃልህ ሰላምታ ይገባል ። የረቂቅ የመን ፈስ ቅዱስ ትንፋሽ ለሚሆን ትንፋ ሽህም ሰላምታ ይገባል ። መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል አንተ ሐዋርያና የጽድቅ መልአክ ስትሆን ለበዓልህ

Scanned with CamScanner

የተቋጠሩ ሁሉ በመትጋት ይቆዩሀል
ረድም በምትሆን ሰማያዊት ቤት
ሀም የክርስቲያን መሰብሰቢያ ወደ
ምትሆን ቤትህ ፈጥነህ ና ።

፲. ለጉርዔከ ። መልአኩ ቅዱስ ሩፋ
ኤል ሆይ ድምጹ ለሚያስደነግጥ ጉረ
ሮህ ሰላምታ ይገባል ። በትከሻህ ጫፍ
ለተሠራ አንገትህም ሰላምታ ይገባል ።
መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል ሆይ ከት
ጉሃን መላእክት አንዱ እንደ መሆንህ
መጠን መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል ሆይ
ትእዛዘ ጦርህ የንጹሔ ጠላት ዲያብ
ሎሰን ይወጋ ዘንድ የተሰለ የአፍህ
ቀሰት ዘመተር ይሳብ ።

፲፩. ለመታክፍቲከ ። መልአኩ ቅዱስ
ሩፋኤል ሆይ የእሳት መታክፍት ለሚ
ሆኑ ትከሻምችህ ሰላምታ ይገባል ።
በሰማይ ጀርባ ላይ ለተቀመጡ ክንፎ
ችህም ሰላምታ ይገባል ። ሁሉን የም
ታደርግና የምትፈጽም መልአኩ ቅድስ

Scanned with CamScanner

ሩፉኤል ሆይ እኔ ባሪያህም የመንፈስ ቅዱስ እውቀትን ልምላ ።

፲፪. ለዛባንክ ፥ መልአኩ ቅዱስ ሩፉኤል ሆይ ኑበልባልን ለተጐናፀፈ ጀርባህ ሰላምታ ይገባል ። የጥበብ ጮሰብሰቢያ ለተባለው ደረትህም ሰላምታ ይገባል

መልአኩ ቅዱስ ሩፉኤል ሆይ የመሸኑፍ ጋሻንና የተሳለ የረድኤት ሰይፍን ይዘሀ ከነፍሴ ጠላት ዲያብሎስ በቀልን ትቀበል ዘንድ እኔ ባሪያህ አለምንህለሁ ።

፲፫. ለሕፅንክ ። መልአኩ ቅዱስ ሩፉኤል ሆይ ለሚያቃጥለው ኑበልባላዊ ጭንህ ሰላምታ ይገባል ። ከመሬትና ከውሀ ላልተፈጠሩ ጀሮዎችህም ሰላምታ ይገባል ። ጥበብን የተመላህ መልአኩ ቅዱስ ሩፉኤል ሆይ በደል በሽታ እንዳ ያመኝ ከመድኃኒትህ ትቀባኝ ዘንድ ስለኔ ስለባሪያህ እራራ (እዘን) እኔ ችግረኛው ባሪያህም ከሠብትህ ልካፈል ።

Scanned with CamScanner

፲፬. ለመዘርዒከ ። መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል ሆይ አውሬ ዲያብሎስን ለማ ጥፋት ለበረቱ ክንድህ ሰላምታ ይገ ባል ። ያለመለያየት አንድ ለሆነው አር ምህም ሰላምታ ይገባል ። መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል ሆይ አንተ ጥበብን የተ ጐናጸፍህ እንደመሆንህ መጠን የጠቢ ትን ዓይን ሰው ተመስለህ እንደ ፈወስ ከው የዔሞ ስውነት ከኃጢአት ደዌ ትፈወስ ዘንድ ከመድኂኒትህ ቅባት

፲፭. ለእመቅከ ። መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል ሆይ ለተከበረው ክንድህ ሰላ ምታ ይገባል ። በክንቱ ለማይዘረጋው መሀል እጅህ ሰላምታ ይገባል ። ምሥጢ ርን የተመላህ መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል ሆይ የአምላክ አገልጋይ እንደመሆንህ መጠን እኔ ባሪያህ ጠላቴ ሰይጣንን ድል እንድነሳው በየጊዜውና በየሰዓቱ ከከብርህ ክብርን አካፍለኝ ።

፲፮. ለአጽብዒከ ። መልአኩ ቅዱስ

Scanned with CamScanner

ሩፋኤል ሆይ የጠቢትን አይኖች ለፈወሱ ጣቶችህ ሰላምታ ይገባል ። የዓሣ ሐሞትን ለተኳሉ ጥፍሮችህ ሰላምታ ይገባል ። የምሥጢር ባለቤት መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል ሆይ አንተ የዓርባቱ እንሰሳ ወገን ስትሆን የሱሳ ነቢይ ዳንኤልን የመልአክ እጅ እንደዳሰሰው ጣቶችህ አይኖቼን ይዳስሱ ።

፲፯. ለገቦዋቲክ ። መልአኩ ቅድስ ሩፋኤል ሆይ ሁለቱን ክንፎችህ ለተሸለሙ ጐኖችህ ሰላምታ ይገባል የዘወትር ምግብንም ለተመ ሆድህ ሰላምታ ይገባል ። መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል ሆይ ከአእላፍ አለቃ አንተ አንዱ ስትሆን ለሳሚህ ልጅ የውህው መጕደል ርግብ እንደነገራቸው ለኔ ለባሪያህ በጐ ነገርን ንገረኝ ።

፲፰. ለልብክ ። መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል ሆይ ሽንገላንና መንቀፍን ለተወ ልብህ ሰላምታ ይገባል ። የኑስ ማዳንን

Scanned with CamScanner

ለሚያስብ ሐሳብህም ሰላምታ ይገ
ባል ። የድህንት ባለቤት መልአኩ
ቅዱስ ሩፋኤል ሆይ ንጉሥ ከዘጋበት
በኋላ አገልጋይህን ለማዳን በአራት
ቍን እንደተገለጥልህለት ለኔ ለባሪያህም
ተገለጥልኝ ።

፲፱. ለነዋየ ውስጥከ ። መልአኩ ቅዱስ
ሩፋኤል ሆይ አኳኋኑ ለማይታወቅ ውስ
ጣዊ ገንዘብህ ሰላምታ ይገባል ። ከነፋ
ስና ከእሳት ለተፈጠረ እንብርትህም ሰላ
ምታ ይገባል ። መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል
ሆይ ከሰባቱ ሊቃናት አንተ አንዱ ስት
ሆን ፥ የአቤል መሥዋዕት በእግዚአብ
ሔር ፊት እንደከበረ የኔ ጸሎትና
ምስጋና በአንተ ፊት የከበረ ይሁን ።

፳. ሰላም ለሐሞትከ ። መልአኩ ቅዱስ
ሩፋኤል ሆይ እሳት ታጥቆ ለሚታይ
መገብህ ሰላምታ ይገባል ። አንድ በመ
ሆን ለሚታዩ ጭኖችህም ሰላምታ ይገ
ባል ። መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል ሆይ

Scanned with CamScanner

ሐሳባችንን በረከትህን ይቀበላልና ያዕቆብ እጁን በመስቀል ልጆቹን እንደባረከ ሁሉ አንተም የእኛን አንድነት ትባርክ ዘንድ ፈጥነህ ና ።

ፍኖ ፡ ሰላም ለአብራኪከ ። መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል ሆይ ለመስገድ ለተፈጠሩ ጉልበቶችህ ሰላምታ ይገባል ። በእሳት ሠረገላ ለሚሄዱ እግሮችህም ሰላምታ ይገባል ። የትጉሃን መላእክት አለቃ መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል ሆይ ንጹሕ ሆነህ በዕጣን መሥዋዕት ሣራ እንደዳነች እኔም ከመከራ እድን ዘንድ ምስጋናህን ልይ ።

ፍኗ. ሰላም ለስኮናከ ። መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል ሆይ ከአዳም ተረከዝ ለተለየው ተረከዝህ ሰላምታ ይገባል ። ዳግመኛም ለአንተ ተረከዝ ሰላምታ ይገባል ። የእሳታውያን መላእክት አለቃ መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል ሆይ ለፍዳና የከሀዲት ቀን በመጣ ጊዜ ወዳጅ ወዳ

Scanned with CamScanner

ጆን እንዲረዳው እኔን ባርያህን ፊጥነህ እርዳኝ ።

፳፫. ሰላም ዕብል አጻብኢከ መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል ሆይ እንደፋና ለሚያበሩ ጣዖችህ ሰላም እላለሁ ። ለጥፍሮችህም አንዲትን ሳልለይ ሰላም እላለሁ ። መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል ሆይ ትጉሃን መላእክት ልማዳዊ ፍትወትን እንዴት ወደዱ መላእክትስ ሥጋዊ ሥርዓትን እንዴት ፈለጉ እስቲ ይሆን አስረ ድኩህ ንገረኝ ።

፳፬. ለቆምከ ። መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል ሆይ የመልአክ አካል ልኩ ለሚሆን ቁመትህ ሰላምታ ይገባል ። እንደገናም የብርሃኑ ማማር ለሚያበራው መልክህ ሰላምታ ይገባል ። ድንቅ ድንቅ ሥራዎችን የምትሠራ መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል ሆይ ሰውነቴን የሚጣሏት ሁሉ የከርከር ሥራን በጀመሩ ጊዜ በፊቴ የወደቁን ይሆኑ ዘንድ ድንቅ ድንቅ

Scanned with CamScanner

ሥራዎችህን አወራለሁ ።

፳፩. ነዓ ኀቤየ ። ለሁሉም ምሕረትን የምትለምን መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል ሆይ የልቤን ሐሳብ ትፈጽም ዘንድ ሊቃናትን አስከትለህ ወደኔ ና ለሰውና ለእንስሳት ማኅፀንን የምትፈታ አንተ ነህና ። ጥላህም ሙታንን ያነሣል ።

፳፪. አ.እምሰማያት ጸሎታቸውን ለማሳረግ ለጻድቃንና ለሰማዕታት ከሰማይ የምትወርድላቸው የድኩማን ኃይላቸው መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል ሆይ የእኔን የባሪያህን ጸሎት ታሳርግ ዘንድ በእግዚአብሔር ወልድና በእናቱ በማርያም ስም አምልሐለሁ ።

፳፫. ተወኪፈኩ እግዚኦ ድህውን ባለፀጋ የምታደርገው መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል ሆይ በምችለው ልክ የአቀረብኩልህን ይሁን እጅ መንሻዬን ተቀብለህ ። ለእኔ ለባሪያህ ጀሮ ያልሰማውን ዓይን ያላየውን ዋጋ አሰጠኝ ።

Scanned with CamScanner

የመልአኩ የቅዱስ ሩፋኤል ፈጣሪ
ሆይ እኔን ባሪያህን _____ ከመ
ክራ ሥጋ ከመክራ ነፍስ አድነኝ ለዘ
ለዓለሙ አሜን ።



Scanned with CamScanner

ድርሳነ ሩፋኤል

በአብ ስም አምነን አብን ወላዲ ብለን በወልድ ስም አምነን ወልድን ተወላዲ ብለን በመንፈስ ቅዱስ ስም አምነን መንፈስ ቅዱስን ሠራጺ ብለን የመልአኩ የቅዱስ ሩፋኤልን ድርሳን እንጀምራለን

ኢሊሀንም ቃላት የጠቦትን ዓይን በአበራ ጊዜ የወለተ ራጉኤልንም ጋኔን ባወጣ ጊዜ ብርሃናኤል መብርህኤል ከስትናኤል በጎድናኤል አጽሕድናኤል ብሎ ለመልአኩ ለቅዱስ ሩፋኤል የነገረው እግዚአብሔር ነው ።

መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል ሆይ የእኔንም የባሪያሕን ጠላቶች እንደዚሁ አጥፋቸው ።

የአምላክ በር ጠባቂ ቅዱስ ሩፋኤል ሆይ ለአንተ ሰላምታ ይገባል ።

አሳ አንበሪን የምትገሥፅ ቅዱስ ሩፋኤል ሆይ ለአንተ ሰላምታ ይገ

Scanned with CamScanner

ባል ።

ምስጋናን የተመላህ ቅዱስ ሩፋኤል ሆይ ልአንተ ሰላምታ ይገባል ።

ፈጣሪን የምታመሰግን ቅዱስ ሩፋኤል ሆይ ለአንተ ምስጋና ይገባል ።

መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል ሆይ ከማይጣፍጥ አንደበትና ከፀሩ ከመልአክ ሞት ይልቅ ለአንተ ሰላምታ ይገባል ። ቅዱስ ሩፋኤል ሆይ ለአንተ ሰላምታ ይገባል ።

መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል ሆይ እኔን ባርያህን በጧዋት በማታ ጠብቄኝ የወላድ ማፀን እንዲፈታ ስለተሸመ ከጌታ

አዋልጅ ብትኖር ባትኖርም ሩፋኤል አይታጣም በምጥም ጊዜ ሴቶች ሁሉ በባላገር ያሉ መልኩን ያነግታሉ ማየ ፀሎቱን ይጠጣሉ

ቶሎም በፍጥነት ይወልዳሉ

Scanned with CamScanner



Scanned with CamScanner